**ኢይ እማማ -**

**ለሃሌ እናት ለሚዴቅሳ ልጅ**

ከብርሃነ መዋ breemewa@gmail.com

እምቡጥየ  ልጅ - ሃሌ - ጩቅላ

እማማ ፣ብላ - ኢደይ፣ ብላ - ኡማ ፣ብላ - አዮ፣ ብላ

ጡጦ ጥላ ሀሁ -  ስትል በቡ ስትል

እናት ክቡር ባለ ኢጀብ፣ የምትጠበቅ - የምትፈራ

መሆኑን ተማረች ከሀሁ ጋር

ኢይ እማማ

ለፍትህ ቆርጣ የቆመች - የግፍ ካቴና ፈልቅቃ

እርስበርሱ ሲብላላ - ስየን ከእስር አላቃ - የህግን ልዕልና ሊታሳይ

የህግን መሰሪነት ልትቀጭ - እውነት ብላ - ለውነት ቆማ

መሆኑን ተማረች ከሀሁ ጋር

ኢይ እማማ

ለጠያቂ  አልባ - ተጠፍናጊ

ዘመድ  ለሌለው - ድምጽ ለሌለው

ለምን ብሎ ማን አሰረው? - የህግን ልእልና ሊታሳይ

ሀፐስ ኮርፐስ አንቀጽ ጠቅሳ

አንቀጥቅጣ አለሳልሳ - የህግ አንቀጽ ተንተርሳ

ስንቱን ወጣት አስፈትታ - ስእንቱን ደሀ ፋታ ሰጥታ

መሆኑን ተማረች ከሀሁ ጋር

ያች ህጻን - ያች ጩቅላ - ያች ሃሌ

ዛሬማ - ኢይ እማማ

ለሰላም ብላ - ለውነት ብላ - ለህዝብ ብላ - ላገር ብላ

እንደ ጀግናው  - እንደ ማንዴላ

ጥላዋን ፈርቶ፣ መንፈሰዋን ፈርቶ

ቃልዋን ፈርቶ፣ ድምጽዋን ፈርቶ

ተስፋዋን ፈርቶ፣ ሴትዋን ፈርቶ

ዛሬማ - ኢይ እማማ

በህዝብ ፊት ቀና ብላ - ቃሌ ብላ ቃልዋን ሰታ

ስታሸንፍ ስትረታ

ምንተፍረቱን ህግ ረግጦ - ህግ ጥሶ - አፍሮ - ከስሮ

ከረቸማት ሊያጨልማት

ዛሬማ - ኢይ እማማ

ማንዴላም ተምሳሌት ነበር

የነፃነት - የአንድነት

በግፍ የታሰረ - በፍርሃት የታሰረ - ለአንድነት የታሰረ - ለነፀአነት የታሰረ

ኢይ እማማ

አጠናሽው አነበብሽው

ወኔውንና ጀግንነቱን - ድፍረቱንና ተምሳሌቱን - ካቴናውን ሰንሰለቱን

ለአገር ስትይ ለህዝብ ስትይ - ለአንድነት ስትይ - ለውነት ስትይ

ተረከብሽው ተላበስሽው

ኢይ እማማ

የሚዴቅሳ ልጅ - የጨቅላዋ የሃሌ እናት

የኛም እህት - የኛም አክሰት - የኛም ተስፋ - የኛም ስሜት

የተገደሉ የታሰሩ - የተደበደቡ የተሰደዱ - የሰማዕታት - ተምሳሌት

ያባ ጅፋር፣ ያባዶዮ - የነቴዎድሮስ ፣የነአስራት - የነጥላሁን ፣የነደብተራው - የነሸብሬ፣ የነተስፋየ

ለእልፍ አእላፍ - ፍትህ ላጣው ------ ተምሳሌት

የድል ጮራ ብስራት -

የወኔ ኢድባር

የሚደቅሳ ልጅ ------የሃሌ እናት

ኤፕሪል 17፣ 2009
ዋሽንተን ዲሲ